# መምህር ገብረ ሕይወት ሰይፉ

## /፲፰፻፺፱ – ፲፱፻፺፯/



«የኢትዮጵያ ሰው የቀደሙት አባቶች ያቆዩትን ትምህርት አጥብቆ መያዝ አለበት»

ለሰላሣ አምስት ዓመታት ያህል በቤተ ክርስቲያን ትምህርት በየ ጉባኤ ቤቱ አሳልፈዋል:: ከዚያም ከስልሣ ዓመታት በላይ አስተምረዋል:: በዚህ የረጂም ዘመን የመምህርነት ጊዜያቸው ሁሉ ጉባኤያቸው እንደደመቀ ቆይቷል:: ዛሬ በዕድሜ ብዛት እርጅና ቢታገላቸውም እጃቸውን አልሰጡትም:: በደብረ ጽጌ ቅድስት ማርያም ገዳም የመጻሕፍቱ ሊቅ አልጋ ላይ ሆነው ደቀመዛሙርቶቻቸውን ያስተምሩ ነበር:: ከሌሎችም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ምእመናን የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፤ ያብራራሉ፤ ያስረዳሉ::

መምህር ገብረ ሕይወት ሰይፉ የተወለዱት ጳጉሜ ፩ ቀን ፲፰፻ ፺፱ ዓ.ም በድሮው ጎንደር ክፍለ ሀገር በጠለምት አውራጃ ልዩ ስሟ ብልብላ ማርያም ከምትባል ደብር ነው:: ወላጆቻቸው አቶ እንግዳ ወርቅ ወንድአፍራሽ እና ወይዘሮ የተመኙ ፋንታዬ ይባላሉ::





በሕፃንነታቸው ትምህርታቸውን የጀመሩት እዚያው ሰሜን አጽገባ ጊዮርጊስ በሚባል አጥቢያ ነው:: በዚያ አባ ወልደኪሮስ ከተባሉ መምህር ዘንድ ከፊደል ንባብ ጀምሮ እስከ ቅዳሴ ድረስ ተማሩ:: ከዚ ያም እልፍ ብለው ጃንአሞራ ከሚባል ቦታ ከመሪጌታ ይትባረክ ዘንድ ምዕራፍና ጾመድጓ ተምረዋል:: እንደገና ወደ ጠለምት ተመልሰው ሰገነት ማርያም በምትባል ደብር ከመምህር /አለቃ/ ብርሃኑ ቅኔ ተማሩ:: ቀጥሎም አለቃ ወልደ ኪዳን ከሚባሉ መም ህር ዘንድ ቅኔውን አስፋፍተዋል::

በወቅቱ የጎጃምና በጌምድር ሊቀጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ አብር ሃም መዓርገ ዲቁና ተቀብለዋል:: የመጻሕፍቱ ሊቅ /መምህር/ ገብረ ሕይወት ዲቁናቸውን ከተቀበሉ በኋላ በትውልድ አካባቢያቸው ለመቆየት አልፈለጉም::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርቷ ተዝቆ የማያልቅ ማዕዷ ሰፊ ነው:: መምህር ገብረ ሕይወት ከሰፊው የትምህርት ማዕዷ በሰፊው ለመቋደስ ሊቃውንቱን ፍለጋ ከትውልድ አካባቢያቸው ርቀው ሔዱ:: ከአለቃ ቀለመ ወርቅ ውዳሴ ማርያምንና ቅዳሴ ማርያምን፣ ከአለቃ /ሊቄ/ ቀጸላ ወንጌልን ተማሩ::

ጣልያን ኢትዮጵያን ከመውረሩ በፊትና በወረረችበት ጊዜ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ ትምህርታቸውን ቀጥለዋል:: ስመ ጥር ከሆኑት ከመምህር ሰይፈ ሥላሴ ሐዲሳትን በሚገባ ተማሩ:: መምህር ገብረ ሕይወት የሚጠሩትም በእኚሁ መምህራቸው ስም ነው:: መምህራቸው አዲስ አበባ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል በነበሩበት ጊዜም ከእሳቸው አልተለዩም:: ከመምህር ገብረ እግዚአብሔርም ዘንድ ሙሉ ሐዲሳትን ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል:: አቡሻህርን ከዶክተር አለቃ አየለ ዘንድ ጠንቅቀዋል:: ከዚያም በኋላ በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ሐዲሱን እያስተማሩ መጻሕፍተ ብሉያትን ከታላቁ ሊቅ ከመምህር ፊላታዎስና ከመጋቤ ምሥጢር ጌራ ወርቅ አጠናቀዋል::

መምህር ገብረ ሕይወት አዲስ አበባ በማስተማር ላይ እንዳሉ በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም ለጸበል ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በሄዱበት በዚያው ቆይተው ከአለቃ /አባ/ ይትባረክ ዘንድ የደብረ ዓባይን ቅዳሴ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል:: ከደብረ ሊባኖስ ገዳም ተመልሰው ከመጋቤ ሐዲስ ወልደ ሚካኤልና ከአቡነ ዮሐንስ ፍትሐ ነገሥትን፣ ከሊቀ ሊቃውንት ሞገስ ሃይማኖተ አበውን ተምረው ምስጢሩን በማገናዘብ ጠንቅቀው ተረድተዋል::

መምህር ገብረ ሕይወት ሰይፉ ጉባኤያቸውን በተባሕትዎ ለማስ ተማር ስለመረጡ ደብረ ሐዊ ገዳም በመግባት ሥርዓተ ምንኩስናን ከመምህር ገብረ ሥላሴ መዓርገ ቅስናን ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ከዚያም ቁምስናን ከብፁዕ አቡነ እንድርያስና ከብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ተቀብለዋል::

ከ፲፱፻፴፰ ዓ.ም ጀምሮ ማስተማሩን የጀመሩት መምህር ገብረ ሕይወት በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት በኣታ በሚገኘው ትምህርት ቤት በሐዲስና በፍትሐ ነገሥት መምህርነት ተመድበው ለዘጠኝ ዓመታት አስተምረዋል:: በዚህም መጋቤ ሐዲስ ተብለዋል:: ከ፲፱፻፶፪ ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ደግሞ በሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሃገረ ስብከት በሚገኘው ደብረ ጽጌ ቅድስት ማርያም ገዳም ሳይታክቱ አልጋም ላይ ሆነው መጻሕፍትን በማስተማር ቆይተዋል::

እኚህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ በትጋት ባስተማሩባቸው ረጅም ዘመናት ብዙዎችን ጳጳሳትና ታላላቅ መምህራንን አስተምረው ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አበርክተዋል::

ከሊቃነ ጳጳሳቱ መካከል፡ ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ፣ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል፣ ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ፣ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል፣ ብፁዕ አቡነ ኒቆዲሞስ፣ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ/ካልዕ/፣ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ፣ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ፣ ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ይገኙበታል::

ከመምህር ገብረ ሕይወት ዘንድ ተምረው ከወጡት ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መምህራን መካከልም፡ አለቃ ልሳነ ወርቅ /የቅድስት ሥላሴ መምህር/፣ መምህር ዐሐይ፣ መምህር ክንፈ ርግብ፣ መምህር ሐዲስ፣ አለቃ ሐረገ ወይን፣ አለቃ ዓምደ ጽዮን፣ መሪጌታ





አድማሱ፣ መምህር ገብረ ጻድቅ፣ አለቃ ገብረ ጻድቅ፣ መሪጌታ አክሊ
ሉ፣ አለቃ ሲራክ፣ መምህር ሚናስ፣ መምህር ተድላ፣ መሪጌታ ሣህለ
ማርያም፣ አባ ገብረ ጻድቅ፣ መምህር ገብረ ማርያም፣ መምህር
እሸቴ፣ መምህር ጽጌ፣ መምህር ዜና ደገፋው፣ መምህር ጥበቡ ወ/ማር
ያም፣ አባ ሳዕከ ማርያም፣ አባ አፈ ወርቅ ዘነበ፣ መሪጌታ ቀለመወርቅ
ገብረ ኢየሱስ፣ መምህር ልዑል ያሬድ፣ አባ መስፍን፣ መምህር ቃለ
አብ፣ መምህር ዘገብርኤል፣ መሪጌታ ስብሐት መኮንን፣ አለቃ
ተሰማ፣ አባ ዘሚካኤል፣ መሪጌታ ገብረ ሥላሴ፣ አባ ጽጌ ብርሃን፣
መሪጌታ ቃለ ጽድቅ፣ አባ ኃይለ ጊዮርጊስ ፣ መሪጌታ ዘውዴ ተፈራ፣
ቄስ አዘነ፣ መሪጌታ ይትባረክ፣ አጋፋሪ ሐዋዝ፣ መሪጌታ መርዓዊ፣
መሪጌታ ዐቢይ፣ መሪጌታ ገብርኤል፣ መሪጌታ ዘውገ፣ መሪጌታ ገብረ
እግዚአብሔር ኃይሉ፣ መሪጌታ ይኄይስ ተመስገን፣ መሪ ጌታ ገብረ
ኢየሱስ ካሣ፣ መሪጌታ ኃይለ ጊዮርጊስ፣ መሪጌታ ልሳነወርቅ ደሳለኝ
ይገኙበታል::

አባ ገብረ ሕይወት ሰይፉ በማኅበረ መነኮሳቱ ፈቃድ የደብረ
ጽጌ ማርያም ገዳም ኃላፊ በመሆንም ገዳሙን አስተዳድረዋል::

ከእርጅና ጋር ሕመም ቢጫጫናቸውም ብርቱ ነበሩ:: በወቅቱ
አንደበታቸውም ጥርት ያለ ነው:: በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ተጠይቀው
የሰጧቸውን መልሶች እንደሚከተለው ይታወሳሉ::

በዚህ በእርጅና ዘመናቸው ያስተምሩ እንደሆነ ሲጠየቁ «ኃይለ
ቃል እየመረጥኩኝ አስተምራለሁ:: ወንጌሉን፣ ጳውሎስን ግብረ ሐ
ዋርያትን አጥኑ እያልኩኝ አስተምራለሁ:: ቅዳሜ ቅዳሜ እዚያ መማ
ሪያ ቦታ አዳራሽ እዚያ ውስጥ ሆኜ እሑድ እሑድ የሚቀደሰውን
ቅዳሴና ወንጌሉን ቀድሜ አስተምራለሁ:: ሐዋርያውን፣ ግብረ ሐዋርያ
ትን፣ ትርጓሜውን እናስጠናለን:: ስብከቱን፣ ዳዊቱን የሚቀድሱትን
ካህናት እናስተምራቸዋለን:: እንዲህ እያደረጋችሁ እያስተማራችሁ ምእ
መናንን እንድታሰናብቱ እያልን ቅዳሜ ቅዳሜ ሰሞነኞችን ሰብስበን
እናስተምራቸው ነበር:: አሁን ከጊዜ በኋላ ጥያቄ መመለስ ነው እንጂ
ለማስተማር ብዙም አልቻልኩም:: ልጆቼ እየመጡ ጥያቄ ይጠይቁኛል::

ያንን ጥያቄ እመልስላቸዋለሁ:: አሁን ትምህርተ ኅቡአትን ኪዳኑን ተርጉምልን እያሉ እተረጉምላቸዋለሁ፣ አስተምራቸዋለሁ፤ ያሉት አይረሳም::

አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ትርጓሜ መማር የግድ ያስፈልገዋል ብለው ያምናሉ? ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ የሚከተለው ነው:: ከሆነማ መጽሐፉ የሚለው አንድ ካህን ሙሉ ሐዲሳቱን ማወቅ ይገባዋል ይላል:: በአሁን ጊዜ ባይሆን ወንጌሉን እንኳን አራቱን ወንጌል ማወቅ አለበት:: ይህን ሳያውቅ እንዳይቀድስ ነው የሚከለክል:: ቅዳሴውም ይናገራል:: ፍትሐ ነገሥት ይናገራል:: በዲድስቅልያ ላይ ይናገራል:: ሐዋርያትም ያን ወስነዋል:: እና በኢትዮጵያችን ሰው ጠንክሮ አይማርም እንጂ ትምህርቱ የሚያስፈልጋቸው ለቀሳውስት ነው::

ከፍ ያለ ዕውቀት ቀሳውስቱ እንዲኖራቸው ነበር የሚታዘዘው:: ዛሬ ግን በሀገራችን ቀሳውስቱ እምብዛም አይማሩም:: ድጓውን፣ ቅኔውን፣ ዝማሬ መዋሥዕት፣ አቋቋምን ከፍ ያለ ትምህርት የሚማሩ ደብተሮች ናቸው:: የቀሳውስት መምህር እነሱ ናቸው:: እነዛ ደብተሮቹ ቅዳሴ የማይቀድሱ ሰዎች የቀሳውስት መምህራን ናቸው:: በኢትዮጵያ ኪዳኑንም፣ መስተብቁዑንም፣ ሊጦኑንም እንዲህ አድርጉ እያሉ የሚነግሯቸው እነሱ ናቸው:: ነገር ግን መሆን የሚገባው ዋና መምህር መሆን የሚገባቸው ቀሳውስት ናቸው:: እንዴውም ምእመናን ጥያቄ ሲያቀርቡ መልስ መስጠት የማይችሉ ካህናት በየቦታው እየበረከቱ ነው ይባላል::

በየጊዜው ቀደም ቀደም ያሉ ሰዎች መምህራንም በያሉበት ያስተምሩ ነበር:: ይልቁንም ይህ ችግር የመጣው ከግራኝ ወዲህ ነው:: ግራኝ አሥራ አምስት ዓመት ሙሉ ሀገሩን አጠፋው፣ ቤተ ክርስቲያንን አቃጠለ፤ ካህኑን ሁሉ ገደለ:: ከዚህ በኋላ እነ ዐፄ ገላውዴዎስ፣ እነ ዐፄ ሚናስ ቤተ ክርስቲያንን ሠሩና ለጊዜው አገልግሎቱ እንዳይታጐል እያሉ ግብረ ዲቁና እየተማሩ ቀሳውስቱ መቀደስ ጀመሩ:: እና በዚያ ጊዜ ብዙ ትምህርት ተማር እንዳይባል፣ ትምህርቱ ቃለ እግዚአብሔሩ በሰፊው ስለሌለ ቤተ ክርስቲያን ሊዘጋ ስለሆነ ቅዳሴው እንዳይታጐልና ሕዝቡ ክርስትና እንዲነሱ በማለት ያኔ ግብረ ዲቁና እና ቅስና አስተምረው ቶሎ ቶሎ እንዲቀድሱ አደረጉ:: ሁሉም ትንሽ





ግብረ ዲቁና እየተማረ መቀደስ መጣ:: ከፍ ያለ ትምህርት መስፋፋቱ ቀረ:: በኋላም በዚህ ዓይነት ልማድ ሆኖ መጥቷል::

ትምህርት ያስፈልጋል:: ያኔ በማስተምርበት ጊዜ መቼም ቃለ እግዚአብሔርን አውጥቼ ይኸውና ካህናትም እንዲህ ያለ ትምህርት ያስፈልጋችኋል፤ ይሄ ትምህርት እንዲህ ያለ ነው እያልኩ ለካህኑ አስተምራለሁ:: በኢትዮጵያ ደግሞ ክርስቲያኑ ስሙ ነው ክርስቲያን የሚባል እንጂ፣ ክርስቲያንነቱ የጸና አይደለም:: በልማድ ነው ያለው:: ምክንያቱም ምንድነው ክርስቲያን የሚባል ክርስትና ከተነሳ ጀምሮ አድጎ በሚያገባበት ጊዜ በተክሊል አግብቶ ሥጋውን ደሙን እየተቀበለ መኖር አለበት:: ድንገት ኃጢአት ሠርቶ ወይንም ቢሰነካከል እንኳ ንስሐ ገብቶ ሰው ሥጋውን ደሙን መቀበል ነው እንጂ ሥጋውን ደሙን የማይቀበል የኢትዮጵያ ሰው ግን ብቻ ክርስትና ተነስቷል በል ጅነቱ እንጂ ከዚህ በኋላ አጥፍቶ ሲያበቃ ተመልሶ ንስሐ አይገባም:: እንደውም ሥጋውን ደሙን የሚቀበል ሰው የለም፣ ካህናቱ ሲቀድሱ ይኖራሉ እንጂ አሁንማ ሰው ሥጋውን ደሙን የሚቀበል አይገኝም::

ይህን ትምህርት በብዙ ዓይነት አስተምረናል ተቀባይ አላገኘንም:: ሰው ሁሉ ያውቃል ትምህርቱን ይሰማል:: አንድ ሰው ሰባት ጊዜም ቢሆን እየወደቀ በንስሐ እየተነሣ ሥጋውን ደሙን መቀበል አለበት እንጂ አንዴ ኃጢአት ሠርቻለሁ ብሎ አንዴ እንደራቀ መቅረት የለበትም:: ምእመናኑን ለምን እንደዚህ ትሆናላችሁ እያልን ብናስተምራቸው ብንላቸው አይሰሙም:: ያው መቼም ሕዝቡ ልማድ አድርጎታል:: ብቻ ክርስቲያን ነኝ እያለ ያወራል:: በቅዳሴ ላይ ፃኡ ሲባል ሥጋውን ደሙን የማይቀበለው ሰው ሁላ በሙሉ ነው መውጣት ያለበት:: አያስቀድስም:: ወንጌሉ እስኪነበብ ድረስ አስቀድሶ ፃኡ ሲባል ሥጋውን ደሙን የማይቀበል ሰው ሁሉ መውጣት ነው ያለበት:: ልማድ የለምና አይወጣም:: ዝም ብሎ ያስቀድሳል እንጂ ፃኡ ዜማው ትዜማለች እንጂ ዜማ ሆኖ ይቀራል እንጂ የሚወጣ የለም:: «ፃኡ ንዑሰ ክርስቲያን፣ የክርስቲያን ታናናሾች ሥጋውን ደሙን የማትቀበሉ ሁሉ ውጡ» ተብሎ ነው የሚታወጅ::

አንድ ጊዜ የግብጽ ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ የሚባሉ መጥተው ነበር:: በኣታ ቀደሱና ለሰው ሁሉ በሉ ሥጋውን ደሙን ይቀበል አሉ:: አይ አይቀበልም አሏቸው:: እንግዲያውስ ለምን አስቀደሱ? ሰው ልማድ የለውም አሏቸው:: እንግዲያው ለምን ያስቀድሳል ፃኡ ሲባል መውጣት አለበት እንጂ ሙሉ ቅዳሴውን ማስቀደስ የለበትም:: ምን ሲል ተቀመጠ በማለት ተናገሩ:: ሌላ ጊዜ እናስተምራቸዋለን አባታችን ያልተለመደ ነውና ያንን የቀረበልዎትን ያቀብሉ አሏቸው:: የሚል መልስ ሰጥተው ነበር::

*አንዳንድ ምእመናን በልጅነታቸው ሲያስቀድሱ ሲቆርቡ ቆይተው ካደጉ በኋላ ይተዋሉ፤ ለምንድነው የማትቆርቡት፣ በተክሊል የማታገቡት ሲባሉ አይፈቀድም:: ቅስፈት ልታስቀስፉን ነው የሚሉም አሉና እርስዎ ምን ይመክሯቸዋል? በማለት ለተጠየቁት ደግሞ፤* እራሳቸው የፍራቻ ምክንያት ያደረጉት ነው:: አንድ ክርስቲያን ከሥጋውና ከደሙ መለየት የለበትም:: ቀድሞ በተክሊል ተጋቡ ሲባሉ ወላጆቻቸው ደግሞ አይሆንም እኛ ልጃችን አትችልም ይሉ ነበር:: ድሮ ተክሊል አድርጎ ሥጋውን ደሙን መቀበል ነበር እንጂ እንደዚህ ዝም ብሎ የሚሄድ አልነበረም:: ነገር ግን ሥጋውን ደሙን ዝም ብላችሁ ተክሊል አድርሳችሁ ባትቀበሉም ግዴለም ተብሎ የተጀመረበት ጊዜ አለ:: አዲስ አበባ ይህ የተጀመረ ቅድስት ማርያም ነው:: ማነው የፊታውራሪ በየነ ልጅ ጸጋዬ የሚባል ሰው የራስ ጌታ ቸውን ልጅ ሲያገባ ሥጋውን ደሙን ሳያቀብሉ ይህን ተክሊሉን ብቻ አድርሰው ሰደዷቸው:: ከዛ በኋላ በተለይ አዲስ አበባ እንዲህ ከሆነ ምን አለበት ተብሎ ልማድ ሆነ::

በቃ ይሄን ተክሊሉን እንደቆብ የፎቶ ግራፍ መነሻ አድርገው እስካሁን ድረስ ሥጋውን ደሙን መቀበል ቀርቶ ነበር:: አሁን ደግሞ ተከልክሏል ቆርበው በተክሊል ያገባሉ ሲሉ እሰማለሁኝ::

ለአቅመ አዳም ወይም ለአቅመ ሔዋን ስትደርሱ ቁርባኑን ተውት የሚል መጽሐፋዊ ቃል በጭራሽ የለም:: አይገኝም:: ራሳቸው ምእመናን ይተውታል እንጂ ሰው ሁሉ በልጅነቱ ክርስትና ተነሥቶ





ሥጋውን ደሙን ሲቀበል ከኖረ በኋላ አካለ መጠን ሲያደርስ እንደልቡ ነው:: ያፈርስና ዝም ብሎ ትቶ ክርስቲያን ነኝ እያለ ይኖራል:: እንጂ ስታድጉ አፍርሱ የሚል ነገር እንዴት ተብሎ ይደረጋል:: ይልቁኑ ያጸናል እንጂ እንዴት ይፈርሳል:: ተክሊል አድርጎ ሥጋ ወደሙን መቀበል ነው እንጂ ሌላ ነገር አልታዘዘም:: ይህን የሚያዙ ካሉ ክርስ ትና አልገባቸው ማለትኮ ነው::» በማለት እንደመለሱ ይታወሳል::

የመጽሐፍ መምህር ከመሆናቸው ጋር በማያያዝ በጊዜያችን መናፍቃን በቀላል ቋንቋ በማለት አባዝተው መጻሕፍትን እያሠራጩ መሆኑንና እንደውም በመጽሐፍ ቅዱስ «ኢትዮጵያ» የሚለው ቃል እየተለወጠ «ሱዳን» በሚል ስለመተካቱ ሲነገር በታላቅ ቁጭት የሚከተለውን ብለው ነበር::

ነቢያት የተናገሩት፣ ሐዋርያት ያስተማሩት በቀጥታ ይተረጎማል እንጂ ቃሉ አይለወጥም:: ሊቃውንት የጻፉትም እንደዚሁ:: ሐዋ ርያት እንዲያውም አራቱ ወንጌል ቃሉ እንዳይሰረዝ አሞኒዮስ አውሳ ብዮስ የሚባሉ ሊቃውንት አንዳንድ ቃሉን ዘሩን ቆጥረው ዘጠኝ ሺሕ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ነው ብለዋል:: የወንጌሉን ቃል ብቻ:: ሌሎች እንዳያበላሹ በእንዲህ ያለ ቆጥረው መሥመሩን፣ ሐሳቡን፣ ምዕራፉን ጽፈውት ይገኛል:: እና ቃሉ ለምን ይለወጣል? መቼም ሰው በገንዘብ እየተለወጠ የመጣውን ሁሉ ይቀበላል:: የኢትዮጵያ ሰው የቀደሙት አባቶች ያቆዩትን ትም ህርት አጥብቆ መያዝ አለበት::

ሱዳን አሉት? ምን አገናኘቶት:: እንደውም ሱዳን የኢትዮጵያ ግዛት የነበረ አገር ነው:: የእኛ ግዛት ነበረ እንጂ እኛ ለእነሱ ልንገዛ አንች ልም:: መቼም ኢትዮጲስ የካም ዕጣ ነች:: ኢትዮጲስ የሚባል የካም ልጅ መጥቶ ነው ያቀናው:: ከዛ በኋላ ደግሞ የሴም ልጆች የሕርቃ ልጆች አቅንተዋታል ነው የሚባለው:: ስለዚህ ሱዳን የእኛ ግዛት የነበረ ነው እንጂ ምን ሱዳን ያሰኘዋል:: በዚህ ዓይነትማ ወደፊትም የበለጠ ጥፋት እንዳይሠራ ትርጉም እንዳይዛባ ሊቃውንት፣ መምህራኑ፣ ጳጳሳቱ ተሰብስበው ኃይለ ቃሉን አወጣጥተው ባጭሩ ለሕዝቡ የሚገባ ነገር መወሰን አለባቸው::

የኔታ በአሁኑ ጊዜ ግእዝ ሞቷል፡ አገልግሎት አይሰጥም ስለሚሉ ሰዎችና ግእዝ የአዳም ቋንቋ ስለመሆኑ ተጠይቀው እንደሚከ ተለው መልስ ሰጥተውበታል:: ሞቷል? የኢትዮጵያ መጻሕፍት በሙሉ በግእዝ ነው ተጽፈው የሚገኙት:: በአማርኛ የተጻፈው በአዲስ አበባ ዛሬ እንጂ በየታላላቁ አድባራትና ገዳማት ብትሄዱ በግእዙ የተጻፈ እንዳለ ይገኛል:: መቼ ይሞታል:: ዛሬ ቅኔ የሚማር ሰው የለም:: አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ተጠናች ያችን እያወራ በዛ ምክንያት ሐዲ ሳትን ትቶታል:: መቼስ የኢትዮጵያ ቋንቋችን ግእዝ ነበረ፤ ግእዝ ነው ቋንቋችን:: አማርኛው በኋላ ጊዜ በዐፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መን ግሥት ነው የተነሣው ተብሎ ይነገራል:: በእርሳቸው ጊዜ ነው የተነገ ረው ይባላል እንጂ ግእዝ ነው ቋንቋችን የነበረ:: ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከአሁን ድረስ አለ:: ሰው ሁሉ ግእዝ መማር ሲገባው ግእዝ የሚማር የለም:: ያው የቅኔ ተማሪዎች አልፈው አልፈው እየሄዱ ይማ ራሉ:: ሌላው ሰውም አይሰማውም:: ትግሬም ግእዝ ይናገራል:: በትም ህርት ስለማይቃና እንደው ወደ ጉሮሮው እየሄደ አያስተካክለውም:: አሁንም ሆነ ወደፊት ቤተ ክርስቲያን ግእዝን እየተገለገለችበት እን ዴት ይሞታል::

መጀመሪያ ዓለም የተፈጠረበት ቋንቋው ዕብራይስጥ ነው የሚባለው:: የሁሉ ቋንቋ ዕብራይስጥ ነበር:: ነገር ግን ባቢሎን በሚባል አገር አንድ ናምሩድ የሚባል የካም ልጅ ያንጊዜ ነግሦ ከዚያ ላይ ሆኖ የውኃ ፏፏቴ እየሰደደ ዘመዶቻችንን ያጠፋው አምላክ ይኸው ላችሁ ግንብ ሠርተን ወጥተን እንገለዋለን ብለው ባቢሎን ከሚባል ላይ ግንብ ሠሩ:: ግንብ ሲሠሩ አርባ አምስት ሺህ የሚሆን አቀበት ከወጡ በኋላ ሥላሴ አይተው ሰዎች ኃጢአት እንዳይበዛ ባቸውና ከፈጣሪያቸው ተጣልተው ሳይለያዩ እኒህ ሰዎች እንዲህ ያለውን ሥራ መሥራት የጀመሩ በቋንቋ አንድ ስለሆኑ አይደ ለምን? ኑ በቋንቋ እንለያያቸው አሉና ሰባ አንድ ቋንቋ አመጡባቸው:: በዚያን ጊዜ ቀድሞ የሚያውቁት ቋንቋ ጠፋባቸው:: ተለያዩና ግንብ የሚገነቡት <ድንጋይ አምጣ> ሲለው ጭቃ ያመጣለታል:: <ጭቃ አምጣ> ሲለው





ድንጋይ ያመጣለታል:: አልሳካላቸው አለ:: በቋንቋ ተለያዩ:: ሰባ አንዱን ቋንቋ ለሦስቱ ነገድ ተካፍለውታል:: ለነገደ ሴም አሥራ አምስት፣ ነገደ ያፌት ሠላሳ ሁለት፣ ለነገደ ካም ሃያ አምስት ተካፍለ ውታል ይባላል:: በዚያን ጊዜ ነው እንግዲህ ግእዝ የሚባለው የተጠ ገኘው:: ናምሩድ የሚባል የካም የልጅ ልጅ ነው:: ሙሴ እንኳን ምን አለው እንደ ናምሩድ ያለ አርበኛ የለም ነው ያለው::» ሲሉ መልስ ሰጥተዋል::

ሌላው የማይረሳው ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትርጓሜ ቤቶች ተጠይቀው የሰጡት መልስ ነው::

መቼም አንድ ምስጢር ሆኖ ሳለ፣ አንዳንድ ሰው መለያየት አይ ቀርም:: ትንሽ ትንሽ ነው የሚለያየው፤ መቼም የሐዲሳቱን አንድ መምህር ናቸው ያስተማሩት ጐንደር ላይ መምህር ወልደ አብ ወልደ ሚካኤል የሚባሉ አሥራ ሰባት ሰዎች አስተምረዋል:: ከእነዚህ ከአ ሥራ ሰባቱ መምህራን ግማሾቹን ሱዳን አርዷቸዋል /ደርቡሾች/ ይባ ላል:: የተረፉት ስድስቱ የርሳቸው ተማሪዎች

፩ኛ. አለቃ ካሣዬ ይባላሉ:: በዚህ በደሴ ግድሞሽ፣ ግሸን ግድሞሽ እነ አለቃ መንክር የሚባሉትን ያስተማሩ ናቸው::

፪ኛ. በትግሬ ቁህ በሚባል ገዳም ያስተማሩ መምህር ወልደ ሩፋኤል የሚባሉ የሳይንት ሰው ነበሩ::

፫ኛ. በሰሜን በደሴ ማርያም አለቃ ገብረ ማርያም የሚባሉ አስተምረዋል::

፬ኛ. መምህር ወልደ ሚካኤል ዜና ማርቆስ ቦሩ ሂደው አስተምረዋል::

፭ኛ. መምህር ወልደ ጊዮርጊስ የሚባሉ እንጦጦ ራጉኤል ሆነው ሃምሳ ዓመት አስተምረዋል::

፮ኛ. አለቃ ጎሩይ የሚባሉ የእነ ሊቀ ሊቃውንት መሐሪ መምህር ነበሩ:: በኋላ ቤተ መንግሥት የሚባለው ጃንሆይ እልፍኝ ቤት ነበር የሚኖሩት:: የአለቃ አየለ መምህር ናቸው:: እነዚህ ስድ ስቱ ናቸው የመጻሕፍት ቤት መሠረቶች::

የእነዚህ መምህራቸው ወልደ አብ ወልደ ሚካኤል ይባላሉ:: ያስተማሩት ጐንደር ግምጃ ቤት ሁነው ነው:: ያስተማሩበት ዘመን

ሱዳን መጥቶ ጐንደርን ባቃጠለበት ጊዜ ነው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው:: ይኸው ነው እንግዲህ:: እና እነዚያ ያልኳችሁ ሰዎች የርሳቸው ተማሪዎች ናቸው:: ወልደ አብ የሚባሉ የመንዝ ሰው ነበሩ:: እሳቸው አራቱን ጉባኤ አስተምረዋል ጐንደር ላይ:: ሰውዬው የአራት መቶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ካህናት ነበሩ:: እያበሉ እያጠጡ ብሉዩን፣ ሐዲሱን፣ ዚቁን፣ መጽሐፈ መነኰሳትን አስተምረዋል::

ከእርሳቸው በፊት ትርጓሜ አለ:: እንዲህ አድርጎ እንደሳቸው ሰብስቦ ያስተማረ ግን የለም::

ከላይ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ሌላ የኔታ ስለ ቅባቶች ትምህርት እንዲህ ይሉ ነበር::

ወልድ በተ ፀነሰ ጊዜ ይሄውና አርባ ቀን ሲሆነው ከመንፈስ ቅዱስ ተወልዶ የባሕርይ ልጅ ሆነ እያሉ ይቀልዳሉ:: እኛ ግን እሱ የባሕርይ አምላክ ነው:: የተዋሐደውን የለበሰውን ሥጋ ራሱ አከበረው እንጂ መንፈስ ቅዱስን አክባሪ አይሻም፤ ራሱ የተዋሐደውን ሥጋ በተዋሕዶ አከበረ እንጂ በቅባት አልከበረም እንላለን:: እነሱ በቅባት ከበረ ይላሉ:: እዎ ካልተመለሱ መለየት አለባቸው::

ታዲያ የነሱ አንድ መምህራቸው ኤውስጣቴዎስ ይባላል:: ሳንኳ ጊዮርጊስ የሚባል የሜጫ ሰው ነው:: ምን ይላሉ:: ታላቁ ኤውስጣቴዎስ ሃይማኖታቸው ጸጋ፣ ቅባት ነው እያሉ ያስወራሉ:: አውቀው ነው እንጂ የራሳቸው መምህር መምህራኑ ስሙን አውጥተውለታል:: መናፍቅ ኤውስጣቴዎስ ቆረንጮ ተክለ ሃይማኖት ይሏቸዋል:: ያንን የጸጋውን መምህር ቆረንጮ ተክለሃይማኖት የቅባቱን ጋዝሆ ኤውስጣቴዎስ ብለውታል:: እና እነሱ ካፈርኩ አይመልሰኝ ብለው ይለፋሉ እንጂ ቃሉ ትንሽ ነገር ነው:: ይህ መርጡለ ማርያም ብዙው የተዋሕዶ ሀገር ነበር:: ዛሬ መምህራኑ አልቀዋል:: እነ መምህር ፊላታዎስ፣ እነ ቄስ ገበዝ ደሳለኝ፣ እነ መምህር ዘውዱ የሚባሉ የተዋሕዶ ታላላቅ መምህራን ነበሩ ሞተዋል::





በመምህርነታቸውና በብፅዕናቸው ስለሚታወቁት ተማሪያቸው አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ማንነት የተናገሩት ደግሞ የሚከተለው ነበር::

አቡነ ጎርጎርዮስ ከሁሉ ሰው በላይ ንባብ አዋቂ ናቸው:: መቼም ትርጓሜውን በአንድ ጊዜ ግልጽ ነው የሚያደርጉት:: ባሕታዊ ነበሩ:: ያን ጊዜ መቼስ ልብሳቸው ቆዳ ነው:: ባሕታዊ ሆነው ነበር የሚኖሩ:: ሦስት ዓመት ከዚህ ሃገር ተቀምጠው በሦስት ዓመት ሐዲሳትን በሙሉ ተምረው ፈጽመውታል:: በኋላ እኔ ዘንድ ቁጭ ይበሉ ወይ ደግሞ ደብረ ሊባኖስ ይቀመጡ አልኳቸው:: መምህር ወልደ ሚካኤል እኚህ ሰው እዚህ ቢቀመጡልን እንደዚህ ዓይነት ሰው እንዴት ይሄዳል ብለው ይፈልጓቸው ነበር:: አልተቀመጡላቸውም እንጂ::

እነዚህን ሁሉ ሊቃነ ጳጳሳት ያፈሩ፣ እጅግ በርካታ ታላላቅ መምህራንን ያወጡ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ይህን ቃለመጠይቅ ባደረጉበት ወቅት በዕድሜ ዘመናቸው ፍጻሜ ዓይናቸው ደክሞ፣ ክንዳቸው ዝሎ፣ ጉልበታቸው ልሞ አልጋ ላይ ውለዋል::

ይኸም ሆኖ እርጅና፣ ጤና ማጣት፣ የጉልበታቸው መድከምና የአቅማቸው ማነስ ከስልሣ ዓመታት በላይ የዘለቁበትን አገልግሎት ከማስተማር ሥራቸው አላገዳቸውም:: ብርቱ ናቸው:: ተስፋቸውና የእምነታቸው ጥንካሬ እንዳለ ነበር:: ለቤተ ክርስቲያን ያላቸው ምኞት የማስተማር ፍላጐትና ዓላማቸው ለሥራ ታጥቆ እንደተነሣ አፍላ ወጣት ትኩስ ነው፣ ገና አልተነካም ነበር::

አልጋቸው ላይ ሆነው እርጅና ታግሎ ባላሸነፈው ጥርት ባለ አንደበታቸው ከመምህራንና ደቀ መዛሙርት ለሚመጣ ጥያቄ መልስ ይሰጣሉ፤ ያብራራሉ፤ ያስረዳሉ:: የመጻሕፍት ቤት ተማሪዎቻቸውን ወኪል መምህር አስቀምጠው ያስተምራሉ:: ጉባኤያቸው እንደ ደመቀ ነበር:: የዕውቀታቸውን አድማስ የዕድሜ ብዛት ግርጃ ሆኖ አልከለከለውም:: ከሰባና ሰማንያ ዓመታት በፊት የሆነን ነገር አስታውሶ ለመግለጽ መምህር ገብረ ሕይወትን እርጅና አላገዳቸውም:: የማስታወስ ችሎታቸው እንዳለ ነበር::

እኚህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ የወር ደመወዛቸው ብር ሁለት መቶ ብቻ ነው:: ሌላ ተጨማሪ መተዳደሪያ የሚሆን ገቢ የላቸውም:: ለምግባቸው፣ ለልብሳቸውና ለሌሎችም አስፈላጊ ጉዳዮች የወጪዷታቸው ይችው የወር ደመወዛቸው ነች:: ከዚችው ላይ ተማሪዎቻቸውን ለሚያስተምሩ ወኪል መምህራቸው ይደጉማሉ:: ሲታመሙ ለመታከሚያና ለመድኃኒት መግዣ ያወጣሉ:: ምግባቸውን ለሚያሰና ዱላቸው ልብሶቻቸውን ለሚያጥቡላቸው ወጪ ሆኖ የሚከፈለው ከዚሁ በወር ከሚያገኙት በጣም አነስተኛ ክፍያ ነበር::

እንዲህም ሆኖ ግን ሐሳባቸው ትኩረታቸው ጨዋታቸው ሁሉ ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ነው::

መምህር ገብረ ሕይወት ሰይፉ ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ዐረፉ:: ሥርዓተ ቀብራቸውም ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖትን ጨምሮ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተፈጽሟል::

<u>ምንጭ</u>:- ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ሰኔ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም